ስደት

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ አገራችን መስቀለኛ መንገድ እንደምትገኝና ህልውናዋም አደጋ ላይ እንደሆነ በተደጋጋሚ የተገለጠና በገሃድም እየታየ ያለ ጉዳይ ሰለሆነ ለአድማጭ ዘርዘሮ መናገር ለቀባሪ ማስረዳት ነው የሚሆነው። በአገሪቱ ዉስጥ ያለው አፈና፣ ጭቆና፣ መድሎ፣ ዘረኝነት፣ ድህነት፣ የህግ የበላየነት ዕጦት፣የመልካም አስተዳደር አለመኖር፣ እኩል የሆነ የሀብት ክፍፍል አለመኖር እና የመሳሰሉት ችግሮች አገራችን ላለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ገላጭ ክስተቶች ናቸው። እነዚህን ችግሮች ከሰራቸው መንግሎ ለመጣል የተቃዋሚ ድርጅቶች ያላሰለሰ ትግል ቢያደርጉም ህብረት በመጥፋቱ ምክንያት የወያኔ ወሮበላ መንግስት ዕድሜ ሊራዘም ችሎዋል። የችግሮቹ ሰፋተና ጥልቀት የዜጎችን የመኖር ህልዉና ሰላናጋውና ይህንም ተከተሎ የመጣው ተሰፋ መቁረጥ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ለቀው ለመሰደድ ዓይነተኛ ምክንያት ሆኑዋል።

ምንም እንኳዋ ኢትዮጵያውያን በስደት ላይ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ነገር በዓይነ ህሊናቸው ለመቃኘት ቢሞኩሩና ክበደቱንም አስቀድመው ቢያውቁም በአገራቸው ላይ ያለው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ዲሞግራፊያዊ ችግሮች ስር የሰደዱ እና በቀላሉ ሊቀየሩ የማይችሉ መሆኑን ሲያውቁ ተሰፋቸው ይጠፋና ስደትን እንደ አይነተኛ የችግሩ መፍትህ በመቁጠር በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወጣት ወገኖቻችን መሰደድን በመምረጥ ይሄው ዛሬ ለደረሰነበት ውርደት እና መከራ ተዳርገዋል። ወጣቱ ትውልድ ትኩስ ሃይል እንደመሆኑ መጠን አገራችን ኢትዮጵያን ወደተሻለ አቅጣጫ የመምራት ፍላጎትና ብቃት ቢኖረዉም የትግራይ ነጽ አውጭ ድርድት ወጣቱ ለሚጠይቀው መሰረታዊ የለውጥ ምላሽ ዓፈና፣ ጭቆና፣ እስራትና ግድያ በመሆኑና ከዛም አልፎ ወጣቱ ግዜውን በአልባሌ ቦታ እንዲያሳልፍ ሲሰታማቲካሊ በመገፋቱ ኢትዮጵያ አገራችንን ወደ ተሻል ደረጃ የማሻገሩን ሃላፊነት በአግባቡ እንዳይውጣ በመሆኑ ነገሮች ሲከሩበት አገሩን ወገኑን  እና ያደገበትን ህ/ሰብ በመተው  የተሻለ ኑሮ ፈለጋ ጉዞውን ወደማያዉቀው ባዕድ አገር በማድረግ ይህው ዛሬ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሊቢያ እንደ ከብት ሲታረዱ፣ በሳውዝ አፍሪካ በዕሳት ጋይተው ሲሞቱ፣ በየመን መውጫ ቀዳዳ አጥተው በጥይት ሲደበደቡና እንዲሁም በተለያዩ የዓለም ክፋላት ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ሲዋረዱ መንግስት ተብየው ያሳየው ድርጊት አገራችን ተቀርቁዋሪና አለኝታ እንደሌላት ነበር በድጋሚ ያረጋገጠልን። ባንፃሩ ግን የናይጅሪያ፣የዝምባዌ ነና የሌሎች አፍሪካ አገራት በደቡብ አሪካ የተደረገውን ኢሰባዊ ድርጊት በመቃውም ማዕቀብ እና ዲፕሎማሲይዊ ግንኙነቶቻቸውን እንዲሚይቆሙ ነበር ያስገነዘቡት።

በዛሬው ዝግጂታችን ሰደትን እንደ ማህበራዊ ችግር  በማየት እና ችግሩንም ተከትሎ እየደርስ ያለውን መጠነ ሰፊ ሰቆቃ መነሻው ምን እንደሆነና ይህን ችግር ለመቀየር ኢትዮጵያውያን ምን ማድረግ አለብን የሚለውን ለመጠቆም እንሞክራልን።

ወደ ዝርዝር ጉዳዩ ከመግባታችን በፊት ሰደት የሚለውን ሃረግ ትርጉም ምን እንደሆነ ሁሉም የሚያዉቀው ጉዳይ ቢሆነም ለመነሻ ይሆነን ዘንድ ከትርጉሙ እንጀምራለን። ከዛ ዝርዝር ጉዳዮችን በማንሳት ኢትዮጵያዉያን ይህን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ይዘት ያለውን  ችግር ለመቅረፍ ምን ማድረግ አለብን የሚለዉን እናያለን።

<u>ስደት ማለት ምን ማለት ነው?</u>

ስደት የሚለው ቃል ፍች ትርጉም እንዲኖረውና አሁን በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ካለው ሁኔታ ጋር ለማያያዝ እንዲያመች በሁለት ከፍለን ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል።

የመጀመሪያው ስደት በአገር ዉስጥ ከአንድ ክ/አገር ወደ ሊላ ክ/አገር የሚደረግ ስደት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ያለው ስደት ከአንድ አገር ወይንም ከአንድ አህጉር ወደ ሊላ ክ/አለም የሚደረግ ፍልሰት ነው። የዛሬው የጽህፋችን ትኩረት በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው የሰደት ዓይነት ይሆናል ማለት ነው።

የሰው ልጆች አገራቸውን ጥለው በሚሰደዱበት ግዛ በሂዎት ዘመናቸው ያካበቱዋቸውን በርካታ ዕሴቶችን ያጣሉ። ባህላቸውን፣ ቁንቁቸውን፣ወጋቸዉን፣ልምዳቸውን፣ቤተሰባቸውን እና አጠቃላይ ማንነታቸውን ያጣሉ። ሁሉንም ነገር እንደዓዲስ ሀ ብለው ነው የሚጀምሩት ሰለዚህ የሰው ልጅ ይህን ሁሉ ያፈራውን ነገር እንደሚያጣ እያወቀ ለምን ይሰደዳል የሚለው ጥያቃ መመለስ ያለበት ቁልፍ ጥያቃ ይሆናል ማለት ነው። ሠው እንደ ሠው የሚታየውም ሆነ የሚኖረው ተዎልዶ ባደገበትና ከላይ የተጠቀሱተን ሲምቦሊክ ካፒታል በአካበተበት ቦታ ላይ ብቻ ነው የሚሆነው። ሠው ከኖረበት ማ/ሰብ ሲዎጣ ልክ ከባሃር እንደወጣ ዓሳ ነው የሚሆነው። ይሂን ሃረግ አበው ሲያጠናክሩት እንዲህ ብለው ሰንኝያቸውን ይቁዋጥራሉ።

ከአገሩ የወጣ አገሩ እስኪ መለስ፣

ቢጭኑት አህያ ቢለጉሙት ፈረስ፣

የግጥሙ መልክት የስደትን አስከፊ ገጽታ በአጭሩ የሚገልጽ ሲሆን የሰው ልጅም በምንም ዓይንት መልኩም ቢሆን በተሰደደበት አገር ውስጥ ሙሉ ሰው ሆኖ ሊኖር እንደማይችል ነው ግጥሙ በአጭሩ ሊያስረዳን የሚሞክረው። የተሰደደበትን አገር ወግ፣ ባህል፣ቋንቋዋ እና ማንነት መያዝ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው። ምክንያቱም የሰዎች ማንነት የሚገነባው ተወልዶ ባደገበት ህ/ሰብ ዉስጥ ሰለሆነ።

ከዚህ በመቀጠል ወደ ዋናው የጽህፋችን መነሻ ጉዳይ  ወደሆነው ሰደት እንገባለን።

<u>ኢትዮጵያውያን ለምን ከአገራቸው ወጥተው ይሰደዳሉ?</u>

በቀደሙ ግዜያቶች  ኢትዮጵያውያን ለትምህርትና ለተለያዩ ጉዳዮች ከአገር ሲወጡ ከአገር ያሰወጣቸዉን ጉዳይ እንኩዋ በቅጡ ሳያገባደዱ ውደ አገራቸው የሚመለሱበት ሁኔታ ነበር የነበረው። ይህ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ምን ያህል አገራቸውንና ወገናቸውን ይወድ እንደነበር ያሳያል። በአሁኑ ወቅት ግን የሚታየው ከዚህ እውነታ በተቃራኒው ነው። ቁጥሩም እንዲህ እንዳሁኑ የበዛ አልነበረም።

ኢትዮጵያዉያን ለምን አገራቸውን ለቀው ይሰደዳሉ የሚለውን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት አገራችን ኢትዮጵያ የተዋቀረችበትን ሁኔታ ማየት ለግንዛቤ ይጠቅመናል ሰልምንል በአጭሩ ባሁኑ ሰዓት ቋንቋን ማዕከል ያደረገውን የወያኔ አወቃቀር እና እያስከተለ ያለውን መጠነ ሰፊ ችግር እንመልከት።

እንደሚታዎቀው ሁሉ ኢትዮጵያ አገራችን ለዘመናት በነፅነት ክብሩዋን በጠላት ሳታስነካ የቆየች በቸኛዋ አፍሪካዊት አገር እንደሆነች እና ህዝቡዋም የራሱን የማይሰጥ የሰውን የማይነካ ፈርሃዊ እግዚህአቤር ያለው ህዝብ እንደሆነ እንኩዋን ኢትዮጵያውያን ቀርቶ ባዕዳንም የሚያዉቁት ሃቅ ነው። ይች የጥቁር ህዝቦች ፋና ወጊ የሆነች  አገር ለብዙ ጥቁር ህዝቦች ነፅነት የታገለችና በተግባረም አርዓያ የሆነች አገር በአሁኑ ሰዓት ከራስዋ አበራክ በወጡ ጉግ ማንጉጎች ነፅነትዋን እና ክብሩዋን አጥታ ዜጎችዋ በዘር፣በሃይማኖት፣ በቋንቋ ተካለው ልዩነትንና ጥላቻን ብቻ በማራገብ ህልውናዋ አደጋ ላይ የወደቀበት ግዜ ላይ ደርሰናል። በተለይ ደግሞ አማራ የተባለዉን የህ/ሰብ ክፍል እንደጠላት በመፈረጅና እስከ ደርግ ድረስ ያለውን የአገሪቱን ችግር በዚህ ማህበረሰብ በመላከክ የችግሮቹ ሁሉ መንስዔ እንደሆነ በመቁጥር በህ/ሰቡ ውስጥ እንደ ጠላት እንዲቆጠርና በአገሪቱ ውስጥ በፖለቲካው፣ኤኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ተገሎ እና አንገቱን ሰበሮ እዲኖር ተደርጉዋል። ለአማራው መገደል ፣ መጭፍጨፍ፣መታሰር እና መገለል ምክንያቱ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ሆኖ መገኘቱ ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ አገራችን በትግራይ ነፅ አውጭ ድርጅት ሰር ከዎደቀች ግዜ አንሰቶ የአገሪቱዋ ህልውና እና የዜጎችዋ ደህንነት አደጋ ላይ ወድቆል። ለዚህም ተጠያቂው በሰልጣን ላይ ያለው ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ነው።

እስኪ ኢትዮጵያውያንን አገር አሰለቅቀው ሊያሰዱ ይችላሉ ብለን ያሰበናቸውን ሁለት ነጥቦችን እንመልከት። እነዚህም ነጥቦች /ፋክተርስ መገፋት/ፑሽ እና መሳብ/ፑል የሚሉት ይሆናሉ ማለት ነው።

እስኪ የመጀመሪያው ነጥብ እንመልከት:

1. መገፋት/ፑሽ የሚለው ነጥብ ዜጎች አገራቸውን ላይ እንዳይኖሩ የሚያደርጉ የመብት ረገጣወች፣ጭቆናዎች ሲኖሩና ኢትዮጵያውያን ይህን ተጨባጭ ሁኔታ ለመቀየር ያስቸግራል ሲሉና ተስፋ ሲቆርጡ የሚደረግ የሰደት ዓይነት ነው።

ከላይ እንደገለፅነው ኢትዮጵያ አገራችን ቋንቋን ማዕከል ባደረገ ዘጠኝ ክልሎች ተከፋፈላ አንዱ ክልል ከሌላኛው ክልል ምንም ዓይነት ግንኙነትም ሆነ ትሰሰር የሌለውና እንደ ሲስተም የተቀነባበረ ሰራ የማይሰራ ዲስፋንክሺናል በሆነ ስይስተም ተዋቅራ አገሪቱ እንደ አገር መቆም አቅቶት እምትገኝበት ዎቅት ላይ ደርስናል። ዜጎችዋ እርስ በራሳቸው በጥላቻና በጥርጣሬ እየተያዩ ፍቅርና አንድነትን አጥተው ይህው ኢትዮጵያችን አደጋ ላይ ዎድቃለች። ያንድ አገር ህልውና ምሰሶ የሆነው መተማመን ጠፍቶ ዘጎች የጎሪጥ የሚተያዩበት ዎቅት ላይ እንገኛለን። ወያኔ ከመነሻው ጀምሮ ኢትዮጵያ የምትባለው አገር አርቲፊሻልና በተረት ተረት የተፈጠረች አገር ናት ሲል ሞቹ ጠ/ሚኒስተር ተብየው ሲሳለቅበት የነበረ ጉዳይ ነው። ታዲያ እችን በተረት ተረት ተፍጠረች የሚሎትን አገር አፈርሶ በአዲስ አወቃቀር ለትግራይ ነፅ አዉጭ ድርጅት በምትጠቅም መልኩ ማዋቀር ግድ ይላቸው ሰለነበር ይህን ህልማቸው ዕውን አደረጉ። ዜጎች እርስ በእርሳቸው በጥርጣሬ በሚናኮሩበትና በሚጣሉበት ግዜ ትኩረቱን ወደ ወያኔ የሚያደርግ ስለማይኖር የአገሪቱን ሃብትና ሰልጣን በማንአለብኝነት ያለ ተቀናቃኝ ለመቆጣጠር እንዲቻለው ለማድረግ

ነው:: ቁንቁን መሰረት ያደረገው የአወቃቀር ዘዴ በይዘቱ ዲሞክራሲያዊ ሰለአልሆነ ዜጎችን እናንተና እኛ በሚል ከፋፈሎ መድሎን የሚያመጣ ሰለሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ዜጎች እኩል እንዳይታዩ የሚደርግ ሰለሆነ ለሰደት አንዱና ዋናው መጋቢ ችግር ይሆናል ማለት ነው::

ሰው ከፍጥረቱ አንሰቶ እስካሁን ድረስ የራሱን ዓለም መልክ የሚያሲዘው ህ/ሰቡን በተለያዩ ዘዴዎች በመከፋፈል/ካታጎራይዝ በማድረግ ነው:: ለምሳሌ ወንድ፣ሴት፣ወጣት፣ሺማግሌ፣ቀይ፣ጥቁር እያለ ነው የሚከፋፈለው የዚህ ዓይነት/ካታጎሪ ጤነኛና ተፈጥሮዊ ሰለሆነ በህ/ሰቡ ዘንድ ሊያመጣ የሚችለው ችግር አይኖርም::

በአንድ ህ/ሰብ ውስጥ ሊኖር የሚገባው ክፍፍል ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ክፍፍሎች ሲሆኑ ከዚህ የወጣና በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያችን ቁንቁን መሰረት ያደልገ ክፍፍል ለአገራችንና ለዜጎቻችን ህልውና አስጊ ሰለሆነ ይህ ሲስተም ተወግዶ ሌላ ህ/ሰቡን ሊያስተሳሰርና በህዝባችን መካከል መተማመን፣ መፋቀር፣ ሊያመጣ የሚችልና የዴሞክራሲ መብቶች የተጠበቁበት: የህግ የበላይነት የሰፈነባት እና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያ በሌለችበት ሁኔታ ሰደት የማይቀር ጉዳይ የሆናል::

መገፋት/ፑሽ የሚለውን ነጥብ ከሰደት ጋር ምን ግንኙንት እንዳለው የእውቁ እንግሊዛዊ ሶሾለጅስት ቶማስ. ሆ. ማርሻል ቲወሪ ያስረዳናል:: ከፑሽ/መገፋት ጋር ያለወውን ግንኙነት እንመልከት::

ቶማስ ሆ. ማርሻል  ዜግነት በሚለው ቲወሪው እንደሚያስረዳው ከሆነ አንድ ሰው ከምግብ፣መጠጥ እና መጠለያ ውጭ ሦስት የማይገረሰሱ የዜግነት መሰረታዊ መብቶች ማሙላት አለባቸው ይላል::

ቶማስ. ሆ.ማርሻል የማይገረሰሱ ሶስት የዜግነት መሰረታዊ መብቶች ብሎ ያሰቀመጣቸው መብቶች እንደሚከተለው እናቀርባቸዋለን::

ሃ. የሲቭል መብት ብሎ ባስቀመጠው ነጥብ ላይ የመናገር፣የመፅፍ፣የመሰበሰብ እና እንደ ዜጋ በአገሩ ላይ ሃብት ንብረት የማፍራት መብቶችን ያካተተ ሲሆን ይህ ባልተሙላበት ሁኔታ የሰው ልጅ ለመብቱ መታገሉ የማይቀር ሲሆን፣ መብቱ ባልተጠበቀበት ግዜ ደግሞ እንዚህን መብቶች ፈለጋ ወደ ተሻለ ቦታ መሰደዳል እንደአማራጭ ያያል ማለት ነው[1]::

<u>እስኪ የስቭል መብት በሚለው ነጥብ ዉስጥ የተካተቱትን መብቶች እንመልከት::</u>

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ አገራችን የዜጎችዋ መብት በሰፊው የተረገጠበትና መብቱን የጠየቀ ዜጋ ሁሉ ለዕስራት፣ለግድያ፣ ለዉርደትና ለሰነለቦናዊ ጥቃት የተጋለጡበት ወቅት ላይ ደርስናል:: መብታቸውን በጠየቁና እየተደረገ ያለውን አፈና፣ጭቆና፣ መከፋፈል በመቃዎም ብዙ ጋዜጠኞች ፣ጦማሪያንና ታጋዮች ባደረጉት የትንቅንቅ የሙብት ትግል ምክንያት ለዕስር የተዳረጉ አያሌዋች ናቸው:: ህዝባዊ እንቅስቃሴውን ለማፈን ወያኔ የፀረ ሽብር ህግ በሚል ሽፋን መብታቸውን በጠየቁ ዜጎች ላይ የእስር እና የግድያ ዘመቻ በሰፊው ተያይዞታል:: አያሌዎች ይህን የሙብት ረገጣ በመፍራት አገራቸውን እየጣሉ መሰደድን በመምረጥ ይህው ዛሬ በሊቢያ፣ በሳውዲ፣ባሳውዝ አፍሪካ፣በየመን፣በሊባኖስ እና በተለያዩ የአለማችን ክፍል ኢ-ሰብአዊ በሆነ አገዳደል እየሞትን እንገኛልን::

የወያኔ/ኢህአዴግ አባል ያልሆነ እንደ ዜጋ ሃብት ንብረት የማፍራት መብቱን ሲስተማቲካሊ እንዲያጣ ይደረጋል::

ለ. የፖለቲካ መብት: ይህ ሁለተኛው የ ቶማስ ቲ. ማርሻል የሙብት ነጥብ ደግሞ የመደራጀትን፣የመምርጥና መመረጥን መብቶት ያጠቃልላል[2]:

ማንኛውም ዜጋ እንደሚያውቀው ሁሉ የዜጎች የፖለቲካ መብትም እንደማንኛውም መብቶች ሁሉ በአገራችን በወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት በሞኖፖል ለ 24 ዓመታት ተይዞ ዜጎች ይህን መብት ለማስከበር ከወያኔ ጋር የትንንቅንቅ ትግል ይዘዋል:: መንግስት ተብየው የወያኔ/ኢሀአዴግ መንግስት የይስሙላ የምርጭ ትያትሩን በየ 5 ዓመቱ አደርጋለሁ እያለ የዓለም አቀፍን ህ/ሰብ እያታለለ ያለ ቢመስለውም ዕውነቱ ግን ለኢትዮጵያ ህዝብ ግልፅ ነው::  ዜጎች የፖለቲካ፣ የዕምነት እና የሃሳብ ነፅነታቸውን ተገፈው በየእስርቤቱ በሚሰቃዩባት አገር የዜጎች የዴሞክራሲይ መብት ተከበሩዋል ብሎ ማላገጥ ከእቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

---

[1] http://www.dissentmagazine.org/article/t-h-marshalls-citizenship-and-social-class
[2] Ibid

እንደሚሉት አባባል ከበደል ላይ በደል ነው የሚሆነው። ዜጎች የመረጡትን መሾም ያልመረጡትን መሻር እማይችሉባት አገር ላይ እየተኖረ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ጅምር አለ በሎ ማለት በህዝብ ላይ ማላገጥ ነው የሚሆነው።

በኢትዮጵያ ዉስጥ ሰራ ሰርቶ ትዳር መስርቶ የተሻል ሂዎት ለመምራት የማይቻል ሰለሆነና የዜጎች የወደፊት ተስፋ በማይታይባት ኢትዮጵያ እኖራለሁ በሎ የሚሳብ ወጣት እጅግ በጣም ትንሽ ነው። እሱም ከዓለው ስርዓት ጋር ባንድም ሆነ በሌላ መልኩ ግንኙነት ያለው ነው። በኢትዮጵያ ዉስጥ ሰራ ለአማግኘት የዘር ትዋፅኣ ወይንም የወያኔን መንግስት የፖለቲካ አቋም መደገፍ ወሳኝ በሆነባት አገራችን መኖር እጅግ በጣም መራራ ስለሚሆን ወጣቱ ትዉልድ ተስፋ በመቁረጥ የራሱንና የቤተሰቡን ሂዎት ለመቀየር ምርጭው ሰደት ሆኑዋል።

ሐ. የሶሻል መብት የሚለው ደግሞ ትምህርትን፣እኩል የሆነ የጤና አገልግሎት እና እኩል የሆነ የሃብት ክፍፍልን የሚመለከት ጉዳይ ነወ[3]።

ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ዉስጥ እኩልና ደረጃውን የጠበቀ የትምህርት አገልግሎት፣ተገቢ የሆነ የጤና አገልግሎት ማግኘትን እና እኩል የሆነ የሃብት ክፍፍል የማይታይባት አገር ሰለሆነች በአገሬ ዉስጥ የበይ ተመልካች ከምሆን በሰው አገር የሆንኩትን ልሁን የሚለው ዜጋ ቁጥር እጅጉን በዝቶ ይሄው ዛሬ ከደረስንበት የመከራና የዉርደት ዘመን ላይ ደርሰናል።

2. መሳብ/ፑል የሚለው ደግሞ ከላይ ከጠቀስነው ነጥብ በይዘት የሚለይ ነው። በአሁኑ ስዓት አለም በጣም የጠበበችበት የኢንፎርሜሺን አለም ውስጥ እንደመኖራችን መጠን ለነገሮች በጣም የተጋለጥን ሰለሆን የአለምን ጅኦ ፖለቲካንም ሆነ ማንኛውንም ነገር ለማወቅ ሰፊ እድል አለን። ዜጎች የራሳቸውን ሁኔታ ከሌሎች አገር ዜጎች ሁኔታ ጋር በማነፅጽር የተሻለ ኑሮ ፍለጋ መሰደድን ሲመርጡ የሚታይ ፋክተር ነው።

የትግራይ ነፀ አዉጭ ደርጅት እየተከተለው ያለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኢትዮጵያውያንን በአገራቸው ላይ ጥረው ግረው ሰርተው እንዳይኖሩ የሚያደርግ ፖሊሲ ሰለሆነ ዜጎች የሚወዱዋትን አገራቸውን ለቀው እንዲሰደዱ ከዓይነተኛ ምክንያቹ አንዱ ሆኑዋል። ኢትዮጵያውያን መሬታቸውን እየተነጠቁ ለ አረብ፣ለህንድ እና ለውጭ ቱጃሮች ሲሰጥ የ ኢትዮጵያውያን አርሶ አንደፋርሶ የመኖር ተስፋቸውን የቀማና በአገራቸው ላይ የመኖር ህልውናቸውን አደጋ ላይ ሰለዎደቀ ይህን አደጋ ለመታደግ ዜጎች ከአገር መሰደደን እንደመፍትሄ መርጠዋል። የሃብት ክፍፍሉ እጅግ በጣም የተዛባና በሁለቱ ጫፎች ማለትም በጣም ትንሹና የወያኔን ፖለቲካ የሚደግፍው ታጁር በአንድ በኩል የሆነበትና በጣም ብዙውና መናጢው የኔብጤ ደሃ በሌላ በኩል በሆነባት ኢትዮጵያ የዜጎች መሰደድ አይቀሬ እንደሚሆን ነው በዙ ጥናቶች የሚነግሩን። ድህነት በአገራችን ዉስጥ እንደነበረ የሚክድ ዜጋ የለም ነገር ግን በ እኔ አውቅልህ አለሁ እየተመራ ያለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ወይንም የአዲሱ ዴሞክራሲ/ልማታዊ መንግስት የኢኮኖሚ: ፖሊሲ ኢትዮጵያ አገራችንን በቀላሉ ልትወጥው ከማትችለው ችግር ዉስጥ ዘፍቆታል።

ከዚህ በታች  የእውቁን ፈረንሳዊ ሶቺኣሎጂስት የኢሚል ዱርከምን አኖሚ የሚለውን ቲዎሪ ከፑል/መሳብ ከሚለው የስዎች በኢኮኖሚ ዎይንም በድህነት ምክንያት አገራቸውን ለቅው የሚዎጡበትን ምክንያት ለማያያዝ እንሞክራልን። አኖሚ የሚለው ቲዎሪ የሚያመለክተው የአካባቢን ሁኔታ ሲሆን መንግስት ወይንም ህ/ሰቡ በግለሰቦች ግብ ዎይንም ፍላጎት ላይ ተመጣጣኝ የሆነ ማስተካከያ ወይንም እርምጃ ሳይዎስድ ሲቀር የሚመጣ ህ/ሰባዊ ችግር ነው። ባንድ ህ/ሰብ ውስጥ የኑሮው ሁኔታ ካልተሻሻለና ዜጎች በአገራቸው ውስጥ አንጽራዊ ደህንንት፣ሰላም እና ሰርቶ ጥሮ ግሮ መብላት ካልቻለ ውስጡ ተስፋ ከለልው እራሰን መግደል እንደ አንድ ዋና መፍትሄ ነው የሚታየው።

እንደ ኢሚል ዱርከም ጥናት ከሆነ እራሰን ማጥፋት የህ/ሰብ ችግር እንጂ የግለሰብ ችግር አለመሆኑን ነው ያሳየን። ምክንያቱም የግለሰቦች ደህንነት እና ደስታ የሚወሰነው በሚኖሩበት ህ/ሰብ አቅምና ችሎታ ነው ይላል። ከዚህ በተጭማሪ ይላል ኢሚል እራሰን ማጥፋት ከመንግስት ጋር ታያያጅነት ያለው ማህበራዊ እዉነታ ነው ይላል። መንግስት ለዜጎቹ ደህንንት ዋስትና መስጠት ካልቻለ ዜጎች የገጠማቸውን ችግር ለመዎጣት ማንኛውንም ዓይነት አማራጭ መውሰዱ አይቀሬ ነው።

እሚል ዱርከም እራሰን ማጥፋት የሚለው ጥናቱን በሶስት ክፍሎች ከፍሎ ያሳያል። ከዚህ ጽህፍ ጋር ተዛማጅ የሆነውን ነጥብ ብቻ መርጠን እንደሚከተለው እናከርባለን። ሁለቱን ነጥቦች ከዛሬው እርዕሳችን ጋር የተያያዙ ሰለአልሆኑ በዚሁ ጽሁፍ ላይ አንመለከታቸውም። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ለናካተው የፈለግነው ነጥብ ዜጎች ህብረተሰቡ ወይንም መንግስት የዜጎቹን የመኖር

[3] http://www.dissentmagazine.org/article/t-h-marshalls-citizenship-and-social-class

ዋስትና መጠበቅ ሳይችል ሲቀር ሰዎች የሚገጥማቸውን ችግር ለመወጣት የሚዎስዱትን ግላዊ ዉሳኔ ኤጎይሲቲክ ወይንም ግለኝነት በሚል ነጥብ ያስቀምጥዋል::

1. ኤጎይስቲክ/ግለኝንት: ግለስቡ በህብረተሰቡ ዉስጥ ሳይታቀፍ ሲቀር:: ማለትም በህበርተሰቡ ዉስጥ በሚደረጉ ማንኛውም ዓይነት ተግባራት ተሳታፊ ሳይሆን ሲቀርና ግለሰቡ በህ/ሰቡ የተገለለ መሆኑ ሲሠማውና ዋጋቢስ እና እረዳተቢስ መስሎ ሲሰማው እራሱን የማጥፋት ዝንባሌው በጣም ከፍ ያለ ነው ይላል የኢሚል ዱርከም ጥናት[4]::

ይህን የኢሚል ዱርከምን እራሰን የማጥፋት ሳይንሳዊ ጥናት ከኛው አገር ሰደት ጋር የሚዛመድ ነገር ሰለሆነ ይህን ነጥብ ማንሳት ተገቢ መሰሎ ሰለታየንና አገራችን ገጥሙት ላለው ችግር ገላጭ ሰልለሆነ ባጭሩ እንደዚህ ኣቀርበዋለን::

ከላይ እንደገለጽነው የአገራችን ችግር ሰፊና ጥልቅ በመሆኑና መንግስት ተብየው የትግራይ ነፅ አውጭ ድርጂት አገሪቱ የገጠማትን ችግር ለመፍታት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ዜጎች ለችግራቸው መፍትሄ ስደትን እንደ ዓይነተኛ አማራጭ ዎሰደውታል:: ኢትዮጵያውያን እምነት ያላቸው ሰለሆኑና ፈራሂ እግዚአቤር ሰላላቸው በመንግስት ተስፋ ቢቆርጡም በ አምላካቸው ተስፋ ሰለማይቆርጡ እራሰን ማጥፋት እንደ አማራጭ አላዩትም:: ፈጣሪያቸን ተስፋ በማድረግ ለገጠማቸው ችግር መፍትሄ መሰደድን መርጠዋል:: እዚህ ላይ ለማሳየት የፈለግነው ዜጎች ችግሩን ለመፍታት እየዎሰዱት ያለውን አማራጭ ነው እንጂ የዎሰዱት አማራጭ ተክክል ነው እያልነ እንዳልሆነ አንባቢ ዎይንም አድማጭ እንዲያውቅልን እንፈልጋለን::

<u>ይህን አገራችን ገብታበት ያለችውን ችግር ለአንዴና ለመጨረዛ ግዜ ለመፍታት ኢትዮጵያውያን ምን ማድረግ የገባሸዋል::</u>

አገራችን ኢትዮጵያ በዘርፍ ብዙ ችግሮች ዉስጥ ተዘፍቃ እንደምትገኝ ሁሉም ዜጋ የሚያውቀው ሃቅ ነው:: ታዲያ ለዚ ዘርፍ ብዙ ችግር ዘርፍ ብዙ መፍትሄ ያስፈልጋል እና ችግሩን ለመቅረፍ ለአንድ ዎይንም ለተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ የሚሰጥ ሃላፊነት ሰላልሆነ ድርጅቶች ከመቸ ግዜው በበለጠ መልኩ ህበረት ፈጥረው ይህን አገር አድን ትግል መምራት ይጠበቅባችዋል:: በአሁኑ ስዓት ያለው ትግል የፖለቲካ ሰልጣን ጥያቄ ሳይሆን የአገር አድን ትግል ሰለሆነ ይህን ግምት ዉስጥ በማስገባት የአንደነት ሃይሉ አብሮ መስራት ይጠበቅበታል:: ጠላታችን ጠንካራ ሆኖ ሳይሆን የተቃዋሚው ትግል ወደ አንድ መምጣት ሰለአስሸገረ ነው ይህ ጥባብ ቡድን አገራችንን ለ 24 ዓመት ሊገዛ የሻለው::

እንግዲህ ከላይ በሰፋትና በዝርዝር እንደተመለከትነው የሰደትና የሌሎች መጠነ ሰፊ ችግሮች መንስዔው የትግራይ ነፅ አውጭ ደርጅት የሚከተለው የፖለቲካ፣የማህበራዊ እና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሰለሆነ የዚህን ጠባብ ቡድንና ፖሊሲዋቹን ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ገርስሶ በምትኩም የዜጎች እኩልነት መብት የሚረጋገጥባት፣ የህግ የበላይነት የሚኖርባት፣ ፍቅር፣ ሰላም የሰፈነባትና የተረጋጋች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የዜጎችን ሙሉ ተሳትፎ የሚጠይቅ ትግል ሰልሚሆን ኢትዮጵያውያን በሚያምኑበት የፖለቲካ ደርጅት ስር ተደራጅው ያለውን ከፍፍይ ሰርዓት መገርሰስ ግዜው የሚጠይቀው አይነተኛ መፍትሄ ነው:: ይህን የመኖር ዋስትናን የሚያሳጣ ወሮ በላና ተስፋ አስቆራጭ መንግስት በመታገል እንጅ ተስፋ ቆርጦ መሰደድ መፍትሄ አለመሆኑን አምኖ ሰራዓቱን ለመቀየር በሚደረገው ትግል ተሳታፊ ሲኮን ነው ሰደትንም ሆነ ሌሎች የአገራችንን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መቀየር ይሚሻለው:: የመሞት መሞት ለአገሩ፣ ለማንነቱና የተሻለች ኢትዮጵያን ለማምጣት ታግሎ መስዋዕት መሆን የክቡር ሞት ነው::

[4]Suicide: A study in sociology by Emil Durkhiem 1951 s. 14.